መልእክት ስምንት

**ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ምሳ. 1፡2፤ 8፡1-31፤ 9፡10፤ ሮሜ 11፡33፤
1 ቆሮ. 1፡24፣ 30፤ ቆላ. 2፡2-3፤ ኤፌ. 3፡10

**I. የምሳሌ መጽሐፍ እግዚአብሔርን በመገናኘት በኩል ከእግዚአብሔር ስለምንቀበለው ጥበብ አጽንኦት ይሰጣል—1፡2፤ 2፡10፤ 4፡5፤ 9፡10፣ 11፡2፣ 14፡33፦**

ሀ. የምሳሌ መጽሐፍ ርእሰ ጉዳይ በእግዚአብሔር ጥበብ እግዚአብሔርን የመምሰል ኑሮ መኖር ነው—3፡13-18፤ 8፡11።

ለ. የምሳሌ መጽሐፍ ማዕከላዊው ሃሳብ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውን እግዚአብሔርን የመምሰል ኑሮ በምድር ላይ እንኖር ዘንድ ጥበብን መከታተል አለብን የሚል ነው—2፡1-9።

ሐ. ጥበብ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው፦ “እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና፤ ከአፉም እውቀትና ማስተዋል ይወጣሉ”—ቁ. 6።

መ. ጥበብ ከወርቅ፣ ብርና ቀይ ዕንቁ ይልቅ የከበረችና የተሻለች እንዲሁም ከማንኛውም ነገር ይልቅ የምትወደድ ናት—3፡14-15፣ 8፡11፣ 19።

ሠ. በምሳሌ መጽሐፍ የተወሰኑ ክፍሎች የእግዚአብሔር ጥበብ እንደ ማንነት ተገልጿል— 1፡20፤ 3፡19፣ 4፡5-9፣ 8፡1-36፦

1. ይህ እንደ ማንነት የተገለጸው የእግዚአብሔር ጥበብ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአዲስ ኪዳን አማኞች በሙሉ ጥበብ የሆነውን፣ የመለኮታዊ ሥላሴ ሁለተኛውን የሚያሳይ ነው—ማቴ. 11፡19፤ ቆላ. 2፡3፣ 1 ቆሮ. 1፡24፣ 30።
2. “እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን መሠረተ”— ምሳ. 3፡19፦
   ሀ. እግዚአብሔር (ያህዌ) ምድርን የመሠረተው እና ሰማያትን ያጸናው የእግዚአብሔር ጥበብ በሆነው በክርስቶስ ነው—1 ቆሮ. 1፡24።
   ለ. ጥበብ፣ እግዚአብሔር ሁሉን ነገሮች እንደፈጠረበት ዋና ሠራተኛ፣ የእግዚአብሔር ደስታ ነው—ምሳ. 8፡30።
   ሐ. የእግዚአብሔር ሁሉን ነገሮች መፍጠር፣ ጥበብ እና የእግዚአብሔር ደስታ በሆነው በክርስቶስ በኩል የሆነ ነው—3፡19፤ ቆላ. 1፡16-17፤ ዕብ. 1፡2።

**II. ሮሜ 11፡33 ስለ እግዚአብሔር ጥበብ ይናገራል፦ “የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው!”፦**

ሀ. በጥበብ እና በእውቀት መካከል ያለውን ልዩነት ማየት አስፈላጊ ነው—ቁ. 33፦

1. ጥበብ ለማቀድ እና ለዓላማ ነው—ኤፌ. 1፡9፤ 3፡11።
2. ጥበብ በሮሜ 11፡36 “ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና” በሚለው እንደተጠቆመው አንድን ነገር በማስጀመር (በማነሳሳት) ውስጥ ይታያል።
3. እግዚአብሔር ልዩና ብቸኛው አስጀማሪ (አነሳሽ) ነው፦ “ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን!”—1 ቆሮ. 8፡6፦
   ሀ. እግዚአብሔር በእውቀቱ ሳይሆን በጥበቡ ብዙ ነገሮችን አነሳስቷል—ምሳ. 3፡19፤ 8፡12፣ 22-31።
   ለ. እግዚአብሔር ያነሳሳውን ነገር ተግባራዊ ለማድረግ ሲመጣ፣ እውቀቱን ያሳያል።

ለ. የእግዚአብሔር ጥበብ “...እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን፥ ተሰውሮም የነበረው የእግዚአብሔርን ጥበብ ምሥጢር...” ነው።—1 ቆሮ. 2፡7፦

1. እንደ እግዚአብሔር ማዕከል እና ለድሰታችን እንደሆነ እድል ፈንታችን፣ ክርስቶስ ጥልቅ በሆነ ምሥጢር ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው—ሮሜ. 11፡33።
2. በእግዚአብሔር ውስጥ በምሥጢር ውስጥ ያለ ጥበብ አለ፤ ይህ ጥበብ ተሰውሮ ነበረ፣ ከዘመናት በፊትም ለክብራችን አስቀድሞ ተወስኗል—1 ቆሮ. 2፡7።

ሐ. “ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን”—ሮሜ. 16፡27፦

1. በአጽናፍ-ዓለም ባሉ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት፣ እኛ ሁላችን ብቻውን ጥበብ ላለው እግዚአብሔር ክብርን እንሰጣለን።
2. ጥበበኛው እግዚአብሔር፣ ለዘመናት በዝምታ ተጠብቆ በነበረው በምሥጢሩ መገለጥ መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስን ለእኛ ሰጥቶናል፣ እርሱም ያዳነን፣ ዳግም የወለደን፣ በመለኮታዊው ማደሉ በኩል ባለማቋረጥ እየለወጠን እና

እያደለን ያለውን፣ በመጨረሻም እኛን ወደ ክብር ውስጥ በማምጣት የሚያከብረን እና የበኵር ልጁን መልክ የሚያስመስለን ነው—ቁ. 25፤ 3፡24-25፤ 5፡10፤ 8፡16፣ 23፣ 29፤ 12፡1-2።

## III. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው—1 ቆሮ. 1፡24፦

ሀ. በአዲስ ኪዳን እንደማንነት የተገለጸው የእግዚአብሔር ጥበብ እንደ እውነታው ክርስቶስ ነው—ምሳ. 8፡1፣ 12፤ 9፡1፤ ሉቃ. 2፡40፣ 52፤ 7፡35፤ ማቴ. 11፡19፦

1. የክርስቶስ መለኮትነት ጥበብ የተገለጠው ከአካላዊ ልኬቱ እድገት ጋር በተመጣጠነ መንገድ ነበረ— ቆላ. 2፡2-3፤ ሉቃ. 2፡40፣ 52።
2. ማቴዎስ 11፡19 ጥበብ ክርስቶስ እንደሆነ ያመለክታል፦
   ሀ. ክርስቶስ ያደረገው ማንኛውም ነገር በእግዚአብሔር ጥበብ የተደረገ ነበረ፣ ይህም ክርስቶስ ራሱ ነው—1 ቆሮ. 1፡24።
   ለ. ይህም ጥበብ፣ በእርሱ ጠቢብ ሥራዎች፣ ጥበብ በተሞላባቸው አድራጎቶች ጸድቋል ትክክለኛነቱም ተረጋግጧል።
3. በሉቃስ 7፡35 ጌታ ኢየሱስ "ጥበብም ለልጆችዋ ሁሉ ጸደቀች" ብሏል፦
   ሀ. በክርስቶስ የሚያምኑት፣ ክርስቶስን እና ሥራዎቹን የሚያጸድቁ እና ክርስቶስን እንደ ጥበባቸው የሚከተሉ የጥበብ ልጆች ናቸው።
   ለ. የክርስቶስ ሥራ፣ ለጥበብ ሕይወት ግድ የሚሰኙ አድርጎ እኛን እንደ ጥበብ ልጆች ማፍራት ነው።

ለ. "የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና"—ቆላ. 2፡3፦

1. እግዚአብሔር የጥበብና የእውቀት ልዩና ብቸኛው ምንጭ ነው፦
   ሀ. የጥበብን እና የእውቀትን እውነተኛ ምንጭ በእግዚአብሔር ውስጥ ተከታትለን መድረስ አለብን—1 ቆሮ. 8፡6።
   ለ. የጥበብ እና የእውቀት መዝገቦች ሁሉ የተሰወሩት የእግዚአብሔር ምሥጢር በሆነው በክርስቶስ ውስጥ ነው—ቆላ. 2፡2-3።
2. ጥበብ እና እውቀት በክርስቶስ ውስጥ መሸመናቸው የተረጋገጠው በተናገራቸው ቃላት፣ በተለይ ደግሞ በማቴዎስ እና በዮሐንስ ወንጌላት ውስጥ በተዘገበው ነው፦
   ሀ. በእነዚህ ሁለት መጽሐፍት የተዘገበው የጌታ ቃላት ከፍተኛውን ፍልስፍና የያዘ ነው።
   ለ. በጌታ ቃላት ውስጥ ያለው ጽንሰ-ሀሳብ እጅግ ጥልቅ ነው።
3. ጥበብ እና እውቀት በክርስቶስ ውስጥ እንደ መዝገብ ስለታጨቁ፣ ክርስቶስ እስከሌለን ድረስ ጥበብ እና እውቀት ሊኖሩን አይችልም—ቆላ. 1፡27፤ 3፡4፤ 10-11።
4. ጌታን ለመገናኘት ማንነታችንን ካንቀሳቀስን፣ ክርስቶስ ሕይወትን-እንደሚሰጠው መንፈስ፣ መንፈሳችንን እና አእምሮአችንን ይሞላዋል ከዚያም በልምምዳችን በክርስቶስ ውስጥ የተሰወረው ጥበብና እውቀት ይኖረናል—2፡3።

## IV. እንደ አማኞች፣ በክርስቶስ ውስጥ ነን፤ እንዲሁም ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብ ሆኖልናል—1 ቆሮ. 1፡30፦

ሀ. አዲስ ፍጥረት የሆንነው እኛ አማኞች የሆነንው እና ያለን ነገር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከእኛ አይደለም—1 ቆሮ. 1፡30፦

ለ. እንደ ጥበባችን ክርስቶስ ሁሉን-ያካተተ ነው፣ ይህም ከእግዚአብሔር ዘንድ በጽድቅ፣ በቅድስና እና በቤዛነት ለእኛ ጥበብ እየሆነልን ነው—1 ቆሮ. 1፡30፦

1. መለኮታዊውን ሕይወት ለመቀበል በመንፈሳችን ዳግም እንወለድ ዘንድ በክርስቶስ እንደ ጽድቃችን በእግዚአብሔር ጸድቀናል—ሮሜ. 5፡18።
2. በክርስቶስ እንደ ቅድስናችን፣ በነፍሳችን እየተቀደስን ነው፣ ማለትም፣ በአእምሮአችን፣ በስሜታችን እና በፈቃዳችን በመለኮታዊው ሕይወቱ እየተለወጥን ነው—6፡19፣ 22፤ 12፡2፤ 2 ቆሮ. 3፡18።
3. ክርስቶስ እንደ ቤዛነታችን ለሰውነታችን ቤዛነት ነው፣ በዚህም የእርሱ ክቡር መልክ እንዲኖረን በመለኮታዊው ሕይወት በሰውነታችን (አካላችን) እንለወጣለን—ሮሜ. 8፡23፤ ፊልጵ. 3፡21።

ሐ. በ 1ኛ ቆሮ 1፡30 *ከእግዚአብሔር ዘንድ* የሚለው በመተላለፍ (transmission) መንገድ ያለን የአሁን፣ ተግባራዊ እና ልምምዳዊ የሆነን ነገር ያመለክታል፦

1. ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእኛ ጥበብ መሆኑ ለየዕለት ልምምዳችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጥበብ የክርስቶስ ወደ እኛ መተላለፍ እንዳለ ያመለክታል—ቁ. 30።

2. ክርስቶስ እንደ ጥበብ በልምምዳችን የአሁን እና ተግባራዊ ጥበባችን እንዲሆን ከእግዚአብሔር ወደ እኛ ያለማቋረጥ መፍሰስ አለበት።
3. እደላውን ለመቀበል ከጌታ ጋር ከቆየን (ዮሐ. 15፡4-5)፣ ልዩ ልዩ ችግሮችን እና ጉዳዮችን ለመፍታት እንደ ጥበብ ወደ እኛ ይተላለፋል።
4. ከጌታ ጋር አንድ ከሆንን እና እደላውን ከተቀበልን፣ በየዕለቱና በየሰዓቱ እንደ ጥበባችን እንለማመደዋለን እንዲሁም እንደሰተዋለን—1 ቆሮ. 6፡17፤ 1፡30።

## V. በቤተ ክርስቲያን በኩል ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ስልጣናት ትታወቃለች—ኤፌ. 3፡10፦

ሀ. አለቆችና ስልጣናት መልካም እና ክፉ የሆኑ መልአካዊ አለቆችና ስልጣናት ናቸው።

ለ. ኤፌሶን 3፡10 በተለይ የሚያሳው ክፉዎቹን—ሰይጣንን እና የእርሱን መላእክትን ነው፦

1. ሰይጣን የራሱ መንግሥት፣ የራሱ መላእክት እና የራሱ የሚገዛበት ክበብ አለው—ማቴ. 12፡26፤ 25፡41፤ ኤፌ. 6፡12፦

   ሀ. ሰይጣን የሚገዛበት ክበብ በአየር ላይ እና በምድር ላይ ነው—2፡2፤ 1 ዮሐ. 5፡19።

   ለ. የዳንኤል መጽሐፍ በምድር ላይ ያሉ መንግሥታት በሙሉ በአየር ላይ ባለው ሰይጣን አገዛዝ ሥር እንደሆኑ ይጠቁማል—10፡13።

2. በቤተ ክርስቲያን በኩል እግዚአብሔር ጥበቡን የሚያሳው በዋናነት ለሰው ልጆች ሳይሆን የእግዚአብሔር ጠላት ተከታዮች ለሆኑት ለአመጹት መላእክት ነው—ራእ. 12፡7።

ሐ. የሰይጣን አመጽ እንኳ ሳይቀር በእግዚአብሔር ጥበብ ክልል ውስጥ ያለው ነው—ኢሳ. 14፡12-14፦

1. የሰይጣን አመጽ ባይኖር ኖሮ፣ የእግዚአብሔር ጥበብ ሙሉ በሆነ መንገድ መታወቅ አይችልም ነበር።
2. ብዙ የእግዚአብሔር ጥበብ ልዩ ልዩ በሆነ መንገድ፣ ማለትም ልዩ ልዩ በሆኑ መንገዶች እና ገፅታዎች እንዲሁም ከብዙ ጎኖች አንጻር ይገለጥ ዘንድ ሰይጣን ብዙ እድሎችን ፈጥሯል—ኤፌ. 3፡10።
3. በመጨረሻም፣ ሰይጣን፣ የእግዚአብሔር ጠላት ተረግጦ ይገዛል የእግዚአብሔርንም ብዙ ልዩ ልዩ ጥበብ ያውቃል—ቁ. 10።

መ. በእግዚአብሔር የተመረጡት እና የተዋጁ ሕዝቡ የክርስቶስን ብልጥግናዎች ሲካፈሉ እና ሲደሰቱ፣ እነዚህ ብልጥግናዎች ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ያቀናብሯቸዋል፣ በእርሷም በኩል ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያት ላሉት አለቆችና ስልጣናት ትታወቃለች—ቁ. 8-10፦

1. በቤተ ክርስቲያን በኩል ሰይጣን እና መላእክቱ የሚያፍሩበት ቀን እየመጣ ነው።
2. [ሰይጣን እና መላእክቱ] ያደረጉት ነገር በሙሉ ጥበቡን ይገልጥ ዘንድ ለእግዚአብሔር እድልን እንደሰጡት ይገነዘባሉ።

## VI. አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ፣ እንደ የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ መጠናቀቅ በጥበብ የተሞላች ትሆናለች—ራእ. 1፡11፤ 21፡2፤ 9-11፤ 22፡16፦

ሀ. አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ንድፏ የተሠራው እና የተገነባችው "መሠረት ያላትን ከተማ" የሥነ-ሕንጻ ባለሙያ (Architect) እና ገንቢ በሆነው በእግዚአብሔር ነው—ዕብ. 11፡10፦

1. ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ክህሎት ያለው ነዳፊ (designer) እና ታላቅ ብልህ ሠራተኛ እንደሆነ ነው።
2. እንዲህ እንዳለው የሥነ-ሕንጻ ባለሙያ (architect) እና ገንቢ፣ እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ቁሳዊ ከተማን አልነደፈም አልገነባምም—ራእ. 21፡9-11።
3. አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ቁሳዊ ከተማ ናት ብሎ መናገር የእግዚአብሔርን ጥበብ ደረጃ ዝቅ የሚያደርግና እንደ ዘላለማዊው፣ ጠቢቡ ሥነ-ሕንጻ ባለሙያ እርሱን የሚያቃልል ነው—ዕብ. 11፡10።
4. እግዚአብሔር ብዙዎች ለተካተቱበት መገለጡ መንፈሳዊ አካልን ነድፎ ገንብቷል—ራእ. 21፡9-11።
5. በጥበቡ ራሱን ወደ እኛ ማንነት ውስጥ እንደ ሥነ-ሕንጻ ባለሙያ እና ገንቢው በማደል አዲሲቷን ኢየሩሳሌምን ይገነባል—ዕብ. 11፡10፤ 2 ቆሮ. 13፡14፤ ራእ. 21፡2፤ 22፡1-2።

ለ. አዲሲቷ ኢየሩሳሌም መንፈሳዊና መለኮታዊ ነገሮችን የምታመለክት ምልክት እንደሆነች ከተገነዘብን፣ በዚህች ከተማ ያለውን የእግዚአብሔርን ጥበብ ማየት እንጀምራለን—1፡1፤ 21፡9-11።

ሐ. እግዚአብሔር የእርሱ ብዙ ልዩ ልዩ ጥበብ ሙሉ መገለጥ ትሆን ዘንድ እንዲህ ያለችውን ከተማ ንድፍ የሚነድፍ እና የሚገነባ ጠቢብ የሥነ-ሕንጻ ባለሙያ እና ገንቢ ነው—ኤፌ. 3፥10፤ ራእ. 21፥2፣ 9-11።

© 2020 Living Stream Ministry